# ስደትን ታዘብኩት… ትዝብቴ ላልተሰደዱ!

(ሶሎሞን አ.)

***ኢትዮጵያዊ ትልቅና ክቡር ነበር!***

ለአቅመ ስደት ከደረሱት ኢትዮጵያውያን ውስጥ ወደ 46% የሚሆኑት አገራቱን ጥለው ለመሰደድ መነሳታቸውን (Gallup’s Potential Net Migration Index) የተሰኘውን የመረጃ ድረ-ገፅ ይጠቁማል። ይህ ማለት እድሜው ከ15–64 አመት የሚሆነው ኢትዮጵያዊ 51% ሲሆን ይህ በአሃዝ ሲገለፅ ወደ 46 ሚሊዮን ይገመታል። ከዚህ ውስጥ ወደ ግማሽ የሚጠጉ ኢትዮጵያውያን ለመሰደድ ዝግጁ ናቸው ማለት ነው። እንደእውነቱ ከሆነ ስደተኝነት ያዋርዳል፣ ያሳፍራል፣ ያሸማቅቃል ስለሆነም 21 ሚሊዮን በላይ ኢትዮጵያውያን ከመሰደድ ወደኋላ አይሉም ማለት የበለጠ የተዋረዱትና ያፈሩት አገራቸው ላይ እንደሆነ ያምናሉ ማለት ነው። ይህ ሁሉ ኢትዮጵያዊ በተለያዩ ምክንያቶች ይሰደዳል ወይም ለመሰደድ አመቺ ጊዜን እየጠበቀ ይገኛል። በዓለማችን ከ21 ሚሊዮን ሕዝብ በላይ የሚኖርባቸው አገሮች ከ52 አይበልጡም። አዲስ የአኗኗር ስርዓት፣ አዲስ የሞራል ስርዓት፤ አዲስ አስተሳሰብ አዲስ ባህል ይሆናል። ለምሳሌ መንግስታችን ሲለምን፣ ባለኃብቶች ሲለምኑ፣ ድርጅቶች ሲለምኑ፣ ግለሰቦች ሲለምኑ፣ ድሆች ሲለምኑ በመጨረሻ አገራችንን የልመና ባሕል ባለቤት እንዳረግናት ሑሉ አሁን ደግሞ ከባለስልጣን እስከ ተራ፣ ከተማሪ እስከ ጨዋ፣ ኃብታም ደኃ ሳይመርጥ ሁሉም ሲሰደድ ስደት ሌላ አዲስ ባህል ሆኖልናል።

እንደ ኢትዮጵያ በአምባገነናዊ ስርዓት ስር የሚማቅቁ ብዙ አገሮች አሉ። የኛ የስደት ምክንያት ለምን በዛ? ለምን ይህ ሁሉ ሕዝብ ይሰደዳል? መሰደድ ያለበት ሕዝብ ነው ግለሰብ? ለስደት የሚዳርጉ ጉዳዮችስ የቶቹ ናቸው።

ማሩን አምርሮ ወተቱን አጥቁሮ በግፍ ሕዝብን የሚጨቁንን አምባገነናዊ ስርዓት ለመጣል የታገለ ሰው ከዚያም ታግሎ ታግሎ የተሸነፈ እንደሆነ ከእስርና ከሞት ለመዳን ቢሰደድ እውነት አለው።

ሕዝብን ለማገልገል የገባውን ቃል አጥፎ ገንዘብ እያከማቸ፣ ወርቅ እየቀበረ ለራሱና ለተከታዮቹ ምቾት የሚጨነቅ ባለስልጣንና የስርዓቱ ተጠቃሚ ስልጣኑን ሲለቅ በሕግ ላለመጠየቅ አገር ጥሎ ቁርበት ጠቅሎ ቢሰደድ ያምርበታል።

በጉብዝናው ወራት ልቡናው ከትቢት፣ አንደበቱ ሰው ከመበደል፣ እጁ ነፍስ ከመግደል፣ ማንነቱ ከኃጢአት ያልተለየ ሰው ከፍርድ አደባባይ ለመሸሽና ከማህበረሰቡ እንዳይገለል ፈርቶ አገር ጥሎ ቢኮበልል አማራጭ አጥቶ ስለሆነ ይደገፋል።

ባለፀጋ የነበረና የዚህ አለም ገንዘብ ሲሰሩት እንጂ ሲጠፋ አይታወቅምና በከንቱ አባክኖ፣ በየመሸታ ቤቱ ላዝማሪ ለዘዋሪ ረጭቶ ድኃ ከሆነ ግብሩ ያሳፍራልና ቢሰደድ አይከፋም። ተከብሬ በኖርኩበት አገር ተዋርጄ አልኖርም፣ ሰጥቼ በኖርኩበት ምድር ለምኜ አልኖርም ቢልና ቢሰደድ ሃቅ አለው።

ነገር ግን መንግስት በሕዝቡ ላይ የሚያደርሰው ጭቆና፣የመልካም አስተዳደር አለመኖር፣ ሙስና፣ የኑሮ ውድነትና ድኀነት፣ ስራ ማጣት፣ ሃሳብን በነፃነት መግለጽ አለመቻልና በመሳሰሉት በብዙሃን ኢትዮጵያውያን ላይ በተፈጠሩ አገራዊ ጉዳዮች በሚከሰት ተስፋ መቁረጥ ምክንያት አገር ጥሎ መሰደድ ከሕብረተሰባችን ሁለንተናዊ ማንነት ጋር የሚያያዝ አገራዊ ችግር ይመስላል። ችግሩ የርስ በርስ ጦርነት ወይም አካባቢ ላይ የደረሰ የተፈጥሮ አደጋ እስካልሆነ ድረስ የጋራ አገራዊ ችግሮችን ምክንያት አድርጎ አገሪቱ ካላት አምራች ኃይል ወደ ግማሽ የሚጠጋው ለምን አልሰደድ ካለ ሕዝባችን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ያዳበረው አገራዊ ችግር መኖሩን ያሳያል። ለመፃፍ ያሰብኩት ስለ አዲሱ ባሕላችን ስላልሆነ ይህን እተውና “በተስፋ ስደተኞች ሁኑ፣ በመከራ ታገሱ፣ በጸሎት ጽኑ” ስለተባለላቸው ስደተኞች ወገኖቼና በምቾት ስለሚኖሩባት አንድ ኃብታም አገር የታዘብኩትን አብዝቼ አወራኃለሁ።

ኖርዲክ የሚለው ስያሜ ስካንዴኔቪያ ከሚለው ጋር የሚወራረስበት ጊዜ አለ። ሁለቱም ስያሜዎች በሰሜን አውሮፓ ክፍል ለሚገኙ አገሮች የሚታወቁበት ጠቅላይ መጠሪያ ሲሆን በኖርዲክ ግዛት ውስጥ ስምንት የሚሆኑ አገሮች ሲኖሩ ከነዚህ ውስጥ ሶስቱ ማለትም ዴንማርክ፣ ኖርዌይና ስዊድን ባላቸው የባሕልና የቋንቋ ትሥሥር ለብቻቸው የስካንዴኔቪያ አገሮች የሚለውን ስያሜ በመጋራት አንድም ሶስትም ሆነው በሰላም ይኖራሉ። ከዚሕ በተጨማሪ በታሪካዊ ዳራቸው እንደ ፊንላንድ አይነት የአካባቢው አገሮችም ይህን ስያሜ የሚጋሩበት ጊዜም ይኖራል።

ዛሬ በዓለማችን ላይ የአገሮችን የተለያዩ ስኬቶች የሚለኩ በርካታ መስፈርቶች አሉ። የአለማችን አገሮች ለዜጎቻቸው በፈጠሩት ብልፅግና፣ ሰላም፣ ዴሞክራሲ፣ የሰው ልማት(እድገት)፣ በትምህርት አቅርቦትና በመሳሰሉት መስፈርቶች ይወዳደራሉ። በነዚህ መስፈርቶች መረጃዎች ተሰብስበው አገሮቹ ባስመዘገቡት ስኬት የደረጃ ሰንጠረዥ ይወጣላቸዋል። በብዙዎቹ ውድድሮች እነዚህ የስካንዴኔቪያን አገሮች ከመጀመሪያዎቹ ተርታ ጠፍተው አያውቁም በዚህም ምክንያት የስደተኛ መዳረሻ ከመሆን አላመለጡም። ከቅርብ ጊዜ ወዲህም ቁጥራቸው በዛ ያለ ኢትዮጵያውያን ወደነዚህ አገሮች ተሰደው ይኖራሉ ወይም እየተሰደዱ ይገኛሉ።

ማንም ተሰዶ ወደዚህ ክልል ሲገባ መጀመሪያ እጅ መስጠት የሚባል ሁሉም ሰው ጥገኝነት ሲጠይቅ የሚሄድበት መንገድ አለ። አገራችሁ በህገወጥ መንገድ ስለገባሁ ወንጀል ስርቻለሁና የምታረጉኝን አድርጉኝ እንደማለት ነው እጅ መስጠት። ስለሆነም ወደፖሊስ ጣቢያ ሔደህ እጅ መስጠት ይጠበቅብሃል። ታዲያ እንደተገባ እጅ አይሰጥም፤ ከዚያ በፊት የሚሠራ ነገር አለ። ሥራው

ምን መሰለህ? እጅ ከመስጠትህ በፊት፥ ፈረንጆቹ ጥገኝነት እንዲሰጡህ ከፈልግህ መጀመሪያ ጥገኝነት የሚያሰጡ የአገርህ ጉዳዮችን ማወቅና የሚስማማህን መርጠህ ማጥናት አለብህ። ለምሳሌ ኤርትራዊ ከሆንክ ኤርትራዊነትህን ማረጋገጥ ብቻ ጥገኝነት ሊያሰጥህ ይችላል። ሱማሊያዊ ከሆንክም የአልሻባብ አባል አለሞሆንህ ብቻ ጥገኝነት ያሰጥሃል። ኢትዮጵያዊ ስትሆን ግን ጥገኝነት ማግኘት እየጠበበ ይመጣብኃል፤ በፈረንጆቹ አስተሳሰብ አንፃራዊ ሰላም፣ የተረጋጋ ዴሞክራሲ፣ ዜጎች ያለምንም ተፅእኖ ሰርተው የሚኖሩባት አገር ናት ብለው ያምናሉ። ስለሆነም ኢትዮጵያዊ ሆኖ ለመጣው ሁሉ ጥገኝነት ስለማይሰጡ የመኖሪያ ፈቃድ የሚያሰጡ ጉዳዮችን ለይተህ ማወቅ አለብህ።

የምትሰደደው ባመዛኙ አገርህ ላይ መኖር (ለሕይወትህ) አስጊ ሲሆንብህ ወይም ሰርቶ ለመበልፀግ አልመህ ነው። የጉዞውን ውጣ ውረድ አልፈህ ወደዚህ ክልል ከገባህ ቡኃላ ኬዝህን በሶስት መልኩ ልታገኘው ትችላለህ። አንድም ሕይወትህን ለማትረፍ ከተሰደድክ አገርቤት እያለህ እራስህ የነበረህ እንቅስቃሴ ኬዝ ይሆንሃል፤ አንድም እንግዳ ፖለቲከኛ ከሆንክ መጀመሪያ ወደዚህ ክልል ስትገባ በተቀበለህና ባረፍክበት ሰው እርዳታ የኬዝህን ረቂቅ ታገኝና ታጠናለህ ወይም ኬዝን በገንዘብ ከሚሰሩ ሰዎች ተገናኝተህ ልቦለዱን በመግዛት የተሰጠህን ገፀ-ባህሪ ትሽመደዳለህ።

ኬዝህን ለይተህ አውቀህ ከዚያም አጥንተህ ለፖሊስ እጅ ከሰጠህ ቡኋላ አንድ ቀን ወይም ረዘም ያለ ጊዜ የሚፈጅ ቃለ-መጠይቅ ይጠብቅሃል። በዚህ ቃለ-መጠይቅ ወቅት ወለም ዘለም የለም። ቀደም ብለው ወደዚህ አገር ገብተው መኖር ከጀመሩ የአገርህ ሰዎች የሰማኃውንና የሽመደድከውን ወይም በኬዝ አስጠኚዎች በል የተባልከውን እያቀላቀልክ ያለስህተት መወጣት ያንተ ድርሻ ይሆናል። አለበለዚያ ደግሞ የመኖሪያ ፈቃድ በገዛ ስህተት ማጣት ይመጣል። በርግጥ በትክክል ቃልህን ስለሰጠህ የመኖሪያ ፈቃድ ላይሰጥህ የሚችልበት አጋጣሚዎች ብዙ ስለሆኑ ይህን ፈተና ማለፍ በአብዛኛው የእድል ጉዳይ ይመስላል።

አገርህ ውስጥ በከፍተኛ ሙያተኝነት ትሰራ ከነበረና ይህንኑ ለማረጋገጥ በቂ ማስረጃ የምታቀርብ ከሆነ የመኖሪያ ፍቃድ የማግኘት እድልህ ይሰፋል። ዲፕሎማት ከሆንክ፣ ጠበቃ ከነበክ፣ ጋዜጠኛ፣ የዩኒቨርሲቲ አስተማሪ፣ መከላከያ ሰራዊት አመራርና ታዋቂ አይነት ሰው ከነበርክ ከፖለቲካ አመለካከትህ ጋር ተገናዝቦ ባጭር ጊዜ ውስጥ ጥገኝነት የማግኘት የተሻለ ዕድል ይኖርኃል። ከዚህ ውጭ ከሆንክ የግድ በህጋዊ መንገድ ከሚታገሉ የፖለቲካ ድትጅቶች ወይም ነፍጥ አንግተው ከሚታገሉ ድርጅቶች ጎራ በአባልነት ወይም በደጋፊነት መሰለፍ ይኖርብሃል። ቀድሞውኑ በዚህ መንገድ የመጣህ ከሆነ እሰየው ነው የኬዝ ጥናቱ ቀለል ይልልኃል። ይቀርልኃል አይደለም ያልኩህ፤ ኬዝ መረጣውና ሽምደዳው ይቀርልህና ክለሳ ብቻ ይሆናል ያንተ ስራ።

ታዲያልህ አንዳንዱ እዛ አዲስ አበባ (አገር ውስጥ) እያለ በሃገሪቱ ውስጥ ምን እየተኪያሄደ እንዳለ ቀርቶ በአጋጣሚ እንኳን በቅርብ የሚያገኛቸውን ጋዜጦች አስተውሎ የማያውቅ ይሆንና፤ እንዲሁ በእለት ተእለት የኑሮ ሂደት ተጠምዶ ወይም ፖለቲካን በሩቁ ከሚሉ ትውልዶች ተጠግቶ ኖሮ ልክ ከአገር ሲወጣ ኬዝ ከፊቱ ይደቀናል። የፖለቲካ እንግዳ ይሆናል። የፖለቲካን ሃሁ እንዲጀምር ይገደዳል። አገርቤት እያለ እንቅስቃሴ ያደርግ የነበረው ደግሞ ከመረጠው ኬዝ ጋር አሳማኝ ቁርኝት ለመፍጠር ይሞክራል። እንግዳው ፖለቲከኛ እንደመጣበት አካባቢና ብሄር የተለያዩ የኬዝ ምርጫዎች ይቀርቡለታል ኤርትራዊ መሆንን ጨምሮ። ኢትዮጵያዊነቴ ያኮራኛል ካለ ደግሞ ነፍጥ አንግተው ወይም በሰላማዊ መንገድ መንግስትን ለመጣል ሚታገሉት የፖለቲካ ድርጅቶች ለምርጫ ይቀርቡለታል።

አስበው እስቲ ኢትዮጵያ ውስጥ ስትኖር ፖለቲካ አያገባኝም ትልና ትበላለህ፣ ትጠጣለህ፣ ትሰራለህ ትኖራለህ። ጥሩ ኑሮ ስትኖር ስትኖር አንድ ቀን ወደውጭ መሔድ ያምርሃል።

ለምን ያምረኛል? ካልከኝ ምናልባት አንተም የስደቱ ባህል ሰለባ ሆነህ፣ ወይ ከውጭ የመጣ ሰው አይተህ፣ ወይ ኑሮሕ ባለህበት ሒድ ሲሆንብህ ወይ ከጎንህ አንዱ ሔዶ ተሳካለት የሚል ወሬ ሰምተህ ወይ ስደትን የሚያበረታታው መንግስትህ በኢቲቪ የተሳካላቸውን ዲያስፖራዎች የህይወት ታሪክ ሲያስኮመኩምህ በቃ በአንዱ ወይም በሌላ ምክንያት መውጣት ያምርህና ትወጣለህ። ያውም በርከት ያለ ገንዘብ ከፍለህ፣ ያውም ሚስትህን፣ ልጅህን፣ የምትወዳቸውን ቤተሰቦችህን ጥለህ እንደሰው ወደማትቆጠርበት ምድር በድግስ ትሸኛለህ። አስተውል ልትማር አይደለም የምትሰደደው ልትሰራ ነው፣ ይታይህ የመኖሪያ ፍቃድ የለህም ገና ጠይቀህ ነው መኖር የምትጀምረው።

ጥገኝነት ለመጠየቅ ፖሊስ ጣቢያ ሄደህ እጅ ወደላይ አድርገህ ጫማህንና ሱሪህን እያስወለቁ ሲፈትሹህ በቃ ያንተ ነገር ከራስህ ይወጣና ወደማታውቀው እድልህ ያዘግማል። ምን ያነበብክ ምን የተማርክ ብትሆን ከዚህ ቀን ቡሃላ የሚሆነው ባንተ ፍላጎት አይደለም። ብላ ሲሉህ ትበላለህ፣ ክፍል ሲሰጡህ ትተኛለህ፣ እንሒድ ሲሉህ ወደመኪናቸው ገብተህ ትቀመጣለህ፣ ቃለመጠይቅ ሲሉህ በፍርሃት ማእበል እየራድክ አስተርጓሚ ተመድቦልህ የሽምደድከውንም ያልተጠየከውንም የባጥ የቆጡን ትቀባጥራለህ።

እጅ ከሰጠህ ቡሃላ ወደስደተኛ መጠለያ ትገባለህ። አባቶችህ ቤተ-እምነቶቻቸውን ሲያንፁ “በተራራ ላይ ያለች ከተማ እንደምን ልትሰወር ይቻላታል” የሚለውን የመፅሃፍ ቃል ይፈፅሙ ዘንድ ተራራን እየፈለጉ ገዳማትና አድባራትን ሲቆረቁሩ እንደኖሩ ሁሉ እዚህም “ከተማን ትኖርበት ዘንድ አንተ ማን ነሕ” እያሉ በተራራና በደን በተዋጠ ገጠራማ ሥፍራቸውን ታደምቅላቸው ዘንድ የሚመሰርቱልህ የስደተኛ መጠለያ ውስጥ ይከቱሃል። በነገራችን ላይ ይህ ቦታ ለፀሎት አመቺ ስለሚሆን የፀሎት መፅሃፍቶችህን ሸክፈህ እንድትሰደድ እመክርሃለሁ።

በመጠለያ ስትኖር እጅ ከሰጠ ከማንም ጋራ እኩል ትሆናለህ። ከማንም እኩል ትደረጋለህ፣ ተመሳሳይ እንክብካቤ ይደረግልሃል፣ ያልተማርክ ከሆንክ ምሁር የመሆን እድል አለህ፤የተማርክ ከሆንክ ዝቅ ብለህ ለመታየት ጥረት ታደርጋለህ። ኢንጅነር፣ ሌክቸረር፣

ጋዜጠኛ፣ ነጋዴ፣ የፈለከውን ብትሆን የራስህ ጉዳይ ይሆናል። እጅ ከሰጠህ በኋላ የምትመኘውን ማንነት ተላብሰህ የሰጠኸውን የፈጠራ ኬዝ መተወን ነው። በዚህ የኑሮህ ክፍል ለኬዝ ሲባል ባዲስ መልክ ተደርሶ ወይም እንደገና ተስተካክሎ ያልተፃፈ የህይወት ታሪክ ማግኘት ይከብዳል። ስለሆነም በዚህ ቦታ ሁሉም ስደተኛ አደገኛ ፖለቲከኛና ቀንደኛ ተቃዋሚ ይሆናል። ትንታኔዎች በየፈርጁ ይኾጎደጎዱልሃል፤ የፖለቲካ ብትል እንደልብ ሞልቷል፣ የኢኮኖሚም ቢሆን ጥራዝ ነጠቅም ቢሆን ትሰማለህ፣ ማሕበራዊውንም እንደዚሁ።

ብሔራዊ ትያትር ቤት አፄ ቴዎድሮስ የሚለው ትያትር ላይ እንድትተውን እድሉን ታገኝና የቴዎድሮስን ገፀባህሪ ይሰጥህና ታጠናለህ። ገብርዬን ወይም ተዋበችንም ልትሆን ትችላለህ፤ እንደኬዝህ። ጊዜውን ትጠብቅና በመድረኩ እየተንጎራደድክ ፀጉርህን አንዠርገህ የቋራው ካሳን ትሆናለህ፤ ጀግና ትሆናለህ፤ ዘራፍ እያልክ ትሽልላለህ። ትያትሩ አልቆ ከተጨበጨበልህ ቡኃላ ከመድረክ ትወርዳለህ። ከመድረክ ወርደህም ቴዎድሮስን ሆነህ ከቀረህ ምን ይባላል 'እግዜር ይማርህ!' እንጂ። ደግሞስ ስንቱን እግዜር ይማርህ! ብለህ ትዘልቀዋለህ? ስለዚህ "ሁሉም ሲያብድ ያላበደ ብቻውን ሰባት አመት ያብዳል!" ትልና አንተም ኬዝህን ሆነሕ ትቀራለህ፤ አብሮሕ ያደገው ማንነትህ ተደብቆ ጥገኝነት ለማግኘት ከተፈጠረ የአንድ ወይም የሁለት ሳምንት እድሜ ያለው አዲሱ ማንነት እንደሰው ቆሞ ሲሔድ ታያለህ ይህም በስደት ላይ ስትኖር የሰው-ያለህ እንድትል ያደርግሃል።

በዚህ የኑሮህ ምእራፍ ከሁሉም ጋር እኩል ትደረግና የወደፊት ህይወትህ ባመዛኙ በእድልህ ይወሰናል። እናት አባትህ ያወጡልህ ስም ይደብርህ ከነበር ያኔ እጅህን ስትሰጥ የምትመኘውን ስም ለኬዝህ የሚስማማውን መርጠህ የመውሰድ መብት አለህ። ታዲያ እዚህ ብትመጣና ከሓበሻው ወገንህ ጋር ባስተዋውቅህ ገዳም ነው እንዴ የመጣሁት ማለትህ አይቀርም። በያዝከው የፅሎት መፅሃፍም አትፀፀትም። ሙሴ፣ ዳዊት፣ ያዕቆብ፣ ኤልያስ፣ ሱራፌልና ዳንዔል መአት መአት የጳጳስ ስም ያጋጥምሃል። ኤልሳ፣ ሳራ፣ ሰላም፣ ቤቲ፣ ...። የመረጥከው ወይም የተመረጠልህ ኬዝ በብሔር ተደራጅቶ የሚታገል ድርጅት ከሆነ ደግሞ ስምህን በብሔረሰቡ የሚዘወተር የስም አይነት እንድታደርግ ትመከራለህ። ይህን ስልህ ግን ከዚህ ውጭ የሆኑ ትክክለኛውን ማንነታቸውን ይዘው የሚገቡ የሉም እያልኩህ አይደለም ጥቂት ቢሆኑም አሉ።

በዚህ የሕይወትህ ምዕራፍ ውስጥ ስትኖር የምትወደው ነገር ማግኘት ብርቅ ነው። በዚህ ምዕራፍህ ውስጥ ጥሩ ነገር መፃፍ ከባድ ነው። ከሁሉ ከሁሉ ግን የምትቸገረው ሰው ነው። እዚህ ሰው የለም ወይም ሰው አይሰደድም። አቶ ያሬድ ጥበቡን ታውቃቸዋለህ? አቶ ያሬድ የቀድሞው የኢህዴን ከፍተኛ አመራር አባልና ከዚያም በኋላ የቅንጅት አለምዓቀፍ አመራር የነበሩ ድንቅ ሰው ናቸው። አውራምባ በተሰኘው አገራዊ ጋዜጣ ላይ ጊዜውን በማላስታውሰው ወቅት ቃለምልልስ አድርገው ያነበብኩትን ንግግራቸውን አልረሳውም። "እንደሰውና እንደልብ ወዳጅ አዲሱንና በረከትን የሚያህል ጓደኛ በ23 አመት የስደት ሕይወቴ አሁንም አላገኘሁም። እንደንጀራ ይርቡኛል፣ ሳቃቸው ይናፍቀኛል፣ ቁምነገራቸው ቀርቶብኛል" ነበር ያሉት። ልብ በል የስምኦን ልጅ በረከት ነው የራባቸው፤ የጨጨሆው ታጋይ አዲሱ ነው የናፈቃቸው። ይህ ንግግራቸው አንተን ላይገባህ ይችላል ምክንያቱም እኔንም የገባኝ እያደር ነው፤ የስደት እድሜዬ እየጨመረ ሲመጣ።

ስደት ላይ ትንሽ ስትቆይ መልክህ ብቻ አይደለም የሚወይበው አእምሮህም ጭምር እንጂ። ስደት ላይ ጫወታ ሲያምርህ ዳዊት በመዝሙሩ "አቤቱ... ደግ ሰው አልቋልና..." ያለው ተፈፀመ ብለህ ዝምታን ትመርጣለህ።

በስደት አለም ስትኖር ለወሬ ያለው እሽቅድምድምና ነጠቃ አያድርስ ነው ስለዚህ ዝምተኛ ካልሆንክ ትቸገራለህ። አቶ ያሬድ እንዲህም ገልፀውት ነበር ስደትን፤ "የዝምታዬ ምክንያትማ ስደት ነው፤ አየህ ስደት እንደጠጅ ቤት ነው። አንዴ አግዳሚ ወንበር ላይ ተቀምጠህ ብርሌ ከጨበጥክ ቡኋላ "እንከባበር" ማለት አይቻልም። ልምድ፣ እውቀት መስዋእትነትህ ዋጋ የላቸውም። አፈ ጮሌ አስር አለቃ ሁሉ ይዘረጥጥሃል።" ነበር ያሉት። ሙያና መጠሪያ ስም እንደነገርኩህ ነው፤ መርጠህ ትመኝ የነበረው ላይ ጉብ ወይም ወርደህ እንዘጭ ማለት ነው። አንተ ኢኮኖሚስት ብትሆንና የኢኮኖሚ ትንታኔ የሚያስፈልገው ውይይት ቢከፈት ላንተ ወረፋ ሰጥቶ እውቀትህን የሚካፈል እዚህ አታገኝም። ሁሉም ኢኮኖሚስት ይሆንልሃል። የአርክቴክት ሙያዊ ማብራሪያ ቢፈለግ ማንም ማንንም አያደምጥም። የቀደመውና ድምፁን ከፍ አድርጎ ያወራው አርክቴክት ይሆናል። ምንም ቢነሳ ማንም ከምንም ተነስቶ አንተ እድሜህን የፈጀሕበትን የሙያ ዘርፍ ሊያስጠናህ ይሞክራል። ምክንያቱም ይህ የስደት አለም ነው።

በስደተኝነት ስትኖር ስብሰባ አልፎ አልፎ ልትጠራ ትችላለህ። ስብሰባው የስደተኛ ጉዳይ ከሚመለከተው የመንግስት መስሪያቤት ከመጡ ሰብሳቢዎች ጋር የሚደረግ ይሆንና ለመግባባት ያመች ዘንድ አንድ እንጊልዝ አፍ የሚናገር ያንተው አገር ሰው እንዲያስተረጉምልህ ትመርጣለህ። እንደነገርኩህ ጠጅ ቤት እንኳን እንግሊዝኛን አንተንም አያስከብርህ። ስለዚህ አንድ በራሱ ፍቃድ መፅሃፍ ተርጉሜ አውቃለሁ የሚል ስደተኛ ከጎንህ ይነሳና ትርጉሙን ያወርድልህ ይጀምራል። ትርጉም በስለሺ ይሉኃል ያኔ ነው። ይህን ጊዜ አንድ ነገር አድርግ፤ በኃሳብ ጭልጥ ብለህ ወደ አገርህ ግባ። ሰብሳቢውንም ተርጓሚውንም፤ ሁለቱንም እንዳታዳምጥ። ካደመጥክ አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ! የምትለው ያኔ ነው። ካደመጥከ አለመሰደድ እችል ነበርን? ብለህ ራስህን የምትጠይቀው ያኔ ነው። ካደመጥክ ያገርቤት ጓደኛህ ትዝ የሚልህ ያኔ ነው። ካደመጥክ ያልተሰደዱ ሰዎች አብዝተው የሚያስቀኑህ ያኔ ነው። ምክንያቱም ይሕ የስደት ሕይወት ነው።

ይህ የመጠለያ ሕይወትህ መቼ እንደሚቆም በእውኑ አታውቀውም። እድለኛ ከሆንክ በሁለት አመት ውስጥ ሻል ወዳለ ሕይወት ትሸጋገራልህ፣ በጣም የተሳካልሕ እንደሆነ በአንድ አመት ውስጥ ይቀናህና የባከኑትን የኛን ሰዎች ትገላገላቸዋለህ። እመብርሃን ከጨከነችብህ ደግሞ ብዙ አመታትን ታባክናለህ። የመኖሪያ ፈቃድ ሲከለክሉህ አገራቸውንም ለቀሕ ውልቅ እንድትልላቸው ይነግሩኃል። ራሳቸው ወዳገርህ እንዳይመልሱህ ካገርህ መንግስት ጋር ስደተኛን የመመለስ ስምምነት የላቸውም፤ ስራ እንዳትሰራ ፍቃድ አይሰጡህም፤ ትምህርት እንዳትማር ስምህን ቀይረሃል፣ ደረጃህን ዝቅ አድርገኃል ስለሆነም ከየት እንደምትጀምር ግራ

ይገባኃል ለዚያውም ከፈቀዱልህ። ስለዚህ አንድም እየተኛህ አንድም እያወራህ አንድም እየበላህ የኢትዮጵያዊነት ወዝህን ታጠፋና ብኩን ሆነሕ ትቀራለህ።

የምትሰደደው አንድም ለመኖር ነው አንድም ለመብል ነው። ነፍስህን ለማትረፍም ይሁን የማይሞላውን ሆድ ለመሙላት ስደት አንተነትህን ይፈታተናል፣ ማንነትሕን ይቀይራል፣ ክብርሕን ይነካል። ስለዚህ ብኩን ላለመሆን አትሰደድ። ለሆድ? ይቅርብህ! ከማንስ ትሰደዳለህ?  ማንን ፈርተሕ? መፍራት ካለብህም ሰውን ፍራ። እንዳመጣላቸው የሚናገሩት አቶ መለስ .የመላዕክት ድርጅት ልፈጥር አልችልም ብለው ኢህአዴግን የሰዎች ድርጅት ሊያስመስሉት ቢሞክሩም አትፍራቸው። ስለዚህ በሰውኛ ተሳስተው ቢያስሩህም በኢህአዲግኛ አስበው ይፈቱሃል፣ ከንቱ ሆነህ ከምትቀር አገርህ ላይ ጥረሕ ግረህ ብትበላ፣ ታስረህ በይቅርታ ብትፈታ ይሻልሃል።

*ወተት አንድም ሶስት*
*አገርህ ወተት ናት-አገርህን ናጣት*
*ሌላውን ቢቀሙሁ ባዳቱ ኑርባት*
*እሳት አንድም ሶስት*
*አገርህ እሳት ናት-አገርክን አዳፍናት*
*አንተ ካልኖርክላት- እሳትህ ጠፊ ናት*

**ኖርዌይን በሥሡ!**
ይሕን ሁሉ ካልኩህ በኋላ አሁንም ሳልበድል ተበደልኩ፣ ሳልገድል ሞትኩ፣ የሚደርስብኝ በደል ሰሚ አጣ፣ ህገመንግስት አርቅቆ የሰጠኝ መንግስትም ህገመንግስቱን ቀርቶ አምላክን እንኳ ሊፈራ አልቻለም። የምበላው፣ የምሰራው  በመንግስት መልካም ፍቃድ ሆነ፣ የምኖርበት መሬትና ቤት የእነርሱ ሆነ ያለልክ ነገሱብኝ። እየቆዩም በጣም ጨከኑብኝ። ስለዚህ አገሬን ጥዬ እግሬ ወዳመራኝ ልሰደድ ነው ካልከኝ አሁንም አደራ እንዳትሰደድ ትንሽ ታገስ እልሃለሁ። ግዴለህም እመነኝ በሕይወትህ እስካልመጡብህ ድረስ አትሰደድ።

አደራ እንዳትሰደድ ብዬህ የለ? ታዲያ ለአንድ ሳምንትም ወይም ለሶስት ወር ወጣ ብሎ የመጎብኘት አጋጣሚ ካገኝህ አታቅማማ። ስትመለስ የተሻለ ሰው ስለምትሆን እድሉን ተጠቀም። ከመውጣትህ በፊት አንድ ምክር ቢጤ ልምከርህ፤ ቦሌ ላይ ደህንነቶቹ ሲፈትሹህ ዴሞክራሲ፣ ፍትህ፣ ነፃነት፣ እኩልነት... ገለመሌህን እዛው አስረክብና ና። እዚህ ዴሞክራሲን የሚሰብክ መንግስት ወይም ፓርቲ የለም። ምርጫ አለ፣ ከምርጫ በፊት ክርክር አለ፣ ስለአረጋውያን፣ ስለ ስደተኛ በዛ አነሰ ወይም የተለያዩ ጥቅማ ጥቅም ሲነታረኩ ታያለህ። እዚህ ያልተፃፈ የሚያነብ የለም። ክርስቲያን ቢሆኑም በስም ብቻ ነው። በርግጥ ጥቂት በዕድሜ የገፉ ሰዎች ግራየተጋቡ ስደተኞችን እያስከተሉ ወደቤተክርስቲያናቸው ሲያዘግሙ አልፎ አልፎ ልታይ ትችላለህ። በተቀረ ሃይማኖታቸው ሕገመንግስታቸው ነው። ምርጫ ሲመጣ ማሰር፣ መግደል...ወራዳ ነው እደግመዋለሁ ወራዳ ነው! በሕገመንግስታቸው አልተጻፈም። ያልተፃፈ አይነበብም እዚህ። አበባና ከረሜላ እያደሉ ወደ ጆሮህ ጠጋ ብለው ምረጠን ይሉሃል፣ የምርጫ ቅስቀሳ መሆኑ ነው። ምርጫው አንድ ሁለት ቀን ሲቀረው የምርጫው ቀን አልኮል በየሱፐር ማርኬቱ እንደማይሸጥ ቀድመው ማስታወቂያ ይለጥፉልሃል። ሞቅ ብሎህ እንዳትሳሳት ወይም በሌሎች መብት እንዳትገባ።

እዚህ ጋዜጣ እንደጉድ ነው። ቅዳሜን መጠበቅ አይጠበቅብህም። በየቀኑ እንደምርጫህ ታነባለህ። ለዘብተኝ አክሆንክ በቀይና በአረንጓዴ መካከል ያለ ግራ የተጋባ ግራ ዘመም ጋዜጣህን ማንም አይከለክልህም። ወግ አጥባቂም ከሆንክ በቀይ የተንቆጠቆጠውን ወገኛውን መርጠህ ማንበብ ነው። መረጃ ለሕዝብ ለማድረስ ያለው ውድድር የማይፃፍ ነገር እንዳይኖር ያደረገው ይመስላል። ሁሉም ክስተት ይፃፋል፤ ጠጥታ መኪና ስትነዳ ተያዘች አሪፍ ወሬ ነው። በተለይ ጠዋት ወደ ስራ ሲኬድ ማንበብ አለብህ የሚል ዶግማ ያለ ነው የሚመስለው። ሁሉም ያነባል ሁሉም ለመረጃ ቅብር ነው። ውሸት ነከቷቸው ያማያውቁ ጋዜጦቻቸውን እየኮሞኮሙ መጓዝ ነው። እንዳንተ አገር ጋዜጦች “ለመረጃ ቅርብ ይሁኑ”፣ “ነፃ ፕሬስ፣ ነፃ ሃሳብ፣ ነፃ መንፈስ” ወዘተ...እያሉ አይሸልሉም። በተግባር አድርገውት ትመለከታለሕ። መንግስታቸው ያከብራቸዋል ብቻ ሳይሆን ይፈራቸዋልም። የጋዜጠኝነት ሀ ሁ.ያልገባቸው ብሎ የሚሰድባቸው የመንግስትነት ሀ.ሁ ያልገባው ጠቅላይ ሚኒስትር እዚህ አልተፈጠረም። መረጃ ከፈለጉ ይሰጣቸዋል፣ ከፖሊስ እኩል አደጋዎችና ወንጀሎች በተፈፀሙበት ቦታ ላይ ይገኛሉ።

ልክ መአዛ ብሩ የቅዳሜ ጫወታ ላይ እንግዳ ጋብዛ እንደምታዝናናህ የዚህ አገር ጠቅላይ ሚንስትርና አንዷ የቴሌቪዥን ጋዜጠኛ እየተወያዩ ነው። ሁለቱም በመገረም የሚያወሩት ስለጋዳፊ ነበር። ጋዜጠኛዋ ያማራትን መጠየቅ መብቷ ነው። ጠይቃ ጠይቃ ስታበቃ መጨረሻ ምን እንዳማራት ልንገርህ። ጠቅላይ ሚንስትሩን ከወንበሩ ተነስቶ እንዲቆም አዘዘችው። ተነስቶ ቆመ። እስቲ አንድ ሁለቴ ዝለልልኝ አለችው። አላቅማማም የሚችለውን ያህል ዘለለ። እሷም ተነሳች አምባገነኖች ላይ እያፌዙ እጅ ለእጅ ተያይዘው ዘለሉ። እኔም አቶ መለስ ትዝ አሉኝ። ዘለላው ቀርቶብኝ እጃቸው ይቆረጣል! ወራዳ!ደደብ! ሳይሉ መልስ የሚሰጡበትን ቀን ይቺ ቀልደኛ ጋዜጠኛ አስናፈቀችኝ።

ይሕን ሁሉ ጥሩ ነገራቸውን እያነሳሁ ስነግርህ “እነሱ እኮ ስላደጉ ነው፤ ስራ ስለሚሰሩ ነው” ልትለኝ ትችላለህ። እኔ ግን እልሃለሁ እዛ አገርህ ህዝቡ ሰራተኛ ነው። ሁሉ ጎበዝ ሁሉ ታታሪ ነው። ሁለቱን አገሮች ላነፃፅርልህ፤ አንተ አገር መጥፎው መንግስትህ ነው እዚህ ጥሩው መንግስታቸው ነው። ጥሩ መንግስት መስርቶ ያላደገ አገር የለምና። መልካም አስተዳደር ከተመሰረተ፣ ሙስናና አድርባይነት ከጠፋ ለምን አገር አታድግ? ያንተ አገር ገበሬ ያጣው የስራ ፍቅር አይደለም የሚያሰራው መንግስት እንጂ፣ አንተ አገር ውስጥ ሃብት የማፍራት ፍራቻ ያለው ኢትዮጵያዊ የለም። በኢትዮጵያ ምድር ሰርቶ የበለፀገ ሰው ማግኘት በጣም አታካች ቢሆንም በስርዐት ሰርቶ ሃብታም ለሆነ ሰው ያለህን ክብር አትዘንጋ ።

“የተማሩ ስለሆኑ ነው” ብትለኝ እኔ ደግሞ እንዲህ እልሃለሁ። ርግጥ ነው እዚህ ያልተማረ የለም ሁሉም የፈለገውን መርጦ ተምሯል ወይም ይማራል። ነገር ግን ለመማር ለመማርማ ያንተም አገር መሪዎች ተምረዋል። አገርህን በሁለት ወገን ከድኅነት እንዳትላቀቅ ሰግጠው የያዟት መሪዎችህና ተቀናቃኞቻቸው በሙሉ እዚህ ተማሩ ከምንላቸው ሰዎች የተሻለ እውቀትና ትምህርት አላቸው። ገበሬው አይደለም አገርህን የመካራ ቁልቁለት ውስጥ የጨመራት፤ ያልተማረ የምትለው የህብረተሰብ ክፍል ለድኅነትህ ድርሻ ቢኖረውም ክፉትን፣ ድንቁርናን፣ ኋላ ቀርነትን የሚያባብሱት ተማርን አወቅን ብለው ሪቮሉሽን ያስነሱት፤ እርስ በርስ የተጨፋጨፉት፤ ጫካ ገብተው ነፃ ሊያወጡህ የታገሉት ናቸው። ስለተማሩ ነው በስማቸው ላይ ቅጥያ ማእረግ ለጥፈው እርስበርሳቸው የሚሞጋገሱት።

ፈረንጅ ስለሆኑ ነው ካልክ ደግሞ ሰዎቹ እንደፈረንጅ እንዳይመስሉህ። ወይም አንተ ስለፈረንጅ ማንነት ተሸውደኃል። እዚህ ያሉቱ ይብዛም ይነስም አንድ ነገር ይችላሉ ያቺን የሚችሏትን ነገር ሳያዛንፉ መከወን ነው። ግራ ቀኝ ማየት የለም። ወደፊት ብቻ፣ የተለየ ነገር ሲገጥማቸው እንዳልገጠማቸው ቆጥረው ያልፉታል። ተራ ነገር ያደርጉታል ምክንያቱም አክብዶ ማየት አስቦ መላ መፈየድን ይጠይቃል። ሁል ጊዜ (right click) ማድረግና ከሚመጡት አማራጮች ውስጥ መምረጥ፤ የሚመረጥ ካጡ ባቦሰጠኝ መምረጥና ማመሳሰል።

ሁሉን ነገር የሚያዩት ፊት ለፊት ነው። ወደስራ በሳምንት አምስት ቀን መሄዳቸውን፣ በሳምንት ስድስት ቀን ገበያ መገብየታቸውንም፣ በየጠዋቱ ጋዜጣ ማገላበጣቸውን አይዘነጉትም። አንድ ፈረንጅ ልክ እንደ ሮቦት ነው፤ ከፋሕ ብሎ አይጨነቅም፣ ታመምክ ብሎ አይሰጋም፣ ጠየቅህ ብሎ አይመልስልህም። አንዴ መስራት የሚችላትን ነገር ይማራል ከዚያ እሷኑ ሲደጋግም ይኖርና ጡረታ ይወጣል። ጡረታ ሳይወጣ የሚሞት የለም። ለነገሩ ሞት ብርቅ ስለሆነ እንዲያውም ከጡረታ ቡኋላም ኖረው ኖረው ወደ መጦሪያቸው ገብተው ይቀመጣሉ እንጂ አይሞቱም። አርጅተውም ካንተ ስለሚጠነክሩ ሽር ሽር ስትወጣ እየገላመጡህ ያልፋሉ።

ሰሜን አትላንቲክ ውቅያኖስን ሲሰማሩበት አሳ ብቻ ነው። ከቻይና ቀጥለው በአሳ ምርት ሁለተኛ ናቸው። ጦርነትን ከመዝገበ ቃላታቸው ቢያወጡትም የጦር መሳሪያን በመሸጥ በአለም ስድስተኛ ናቸው። ይልቁንም ነጭዳማ መሬታቸው ሲቆፈር ጥቁርዳማ ይሆናል። ጥቁርዳማ መሬታቸው ሲሸጥ ገንዘብ ይሆናል።ነዳጅ የኢኮኖሚያቸው ዋልታ ነው አሳና የጦር መሳሪያን ጨምሮ። በቃ ገንዘብ እንዲህ ያገኙና የሚፈልጉትን ይገዛሉ። ምግብ ብትል፣ መጠጥ ብትል፣ ልብስ ብትል፣ ቤት ብትል፣ መኪና ብትል፣ ሙዚቃ ብትል፣ ፊልም ብትል ሁሉን ይገዛሉ። ምን ይሄ ብቻ ሃኪም ብትል መሃንዲስ ብትል፣ መካኒክ ብትል ሾፌር ብትል፣ አስተማሪ ብትል ሁሉን ይገዛሉ።

ወደ ዩኒቨርሲቲያቸው ብትገባ ትምህርት በነፃ ትማራለህ። ክፍል ቁጭ ብለህ አስተማሪ ስትጠብቅ የገዙት የሌላ አገር ዜጋ ብቅ ይልልሃል። መምህራኖቹ ከወደምስራቅ ሲሪላንካ፣ ሕንድ፣ ፊሊፒንስ… ከወደ ምእራብ አሜሪካ፣ እንግሊዝ ጀርመን…ከአፍሪካም ጭምር።

አንድ ቀን በሌክቸር ሆል ውስጥ ቁጭ ብለን ያስተማሪውን መምጣት እንጠብቃለን። በዚህ መሃል የእሳት አደጋ ማንቂያ ደውሉ ማቃጨል ጀመረ። እሳት በጣም ያጠቃቸዋል። ቤታቸውን የሚሰሩት እንዳንተ አገር ሃብታም በድንጋይ ወይም በእምነበረድ አይደለም። መሬቱ ስለማይችል እንዳይመስልህ፤ ቁሩን ለመከላከል እንጂ። አርማታና ብረት የሚጠቀሙት ለምሰሶና ለወለል ብቻ ነው ይህም እንደህንፃው ትልቅነት። የተቀረው አንተ ኮርኒስ ከምትሰራበት እንጨትና ማታ ሲደክምህ ከምታርፍበር ፍራሽ ስለሆን ቤታቸው ሲቀጣጠል ችቦ ያስንቃል። የመኖሪያ ቤት የሆነ እንደሆን በቃ እንጨትና ፍራሽ ቆንጆ ቤት ይወጣዋል። ቤታቸው አንዴ መንደድ ከጀመረ እንዳይዛመት እየተከላከሉ ከቦ መሞቅ ነው።

ወደ ደውሉ እንመለስና፤ ሁልጊዜ ደውሉ በሚጮህበት ወቅት የሚደረግ አንድ ስርዓት አለ። ሁሉም ሕንፃውን ለቆ ባስቸኳይ ይወጣና በአቅራቢያው ወዳለ ክፍት ቦታ ይሰበሰባል። አስተማሪው፣ ተማሪው ሰራተኛው አንድ ላይ ተሰበሰብን። ከሕንፃው የወጣው የሰው ብዛት ከሕንፃው ትልቅነት ጋር አይመጣጠንም። ልክ ያገሪቱ ትልቀት ከዜጉቿ ብዛት ጋር እንደማይመጣጠን ማለት ነው። 5 ሚሊዮን ሊሞሉ ትንሽ ይቀራቸዋል። ሰዎቹ እንዳንተ አገር ድሃ እንዳይመስሉህ። ከምድር አንደኛ ሃብታም ናቸው ። ያንተ አመታዊ ገቢ 350 ዶላር ሲሆን ግምታዊ በሆነ ስሌት የነዚህ 240 ጊዜ ያጥፍሃል። 84,443 ዶላር በአመት በአማካኝ ያጋብሳሉ። ድኃ የሚባለው  የሞተር ጀልባ የሌለው ነው። መግዛት አቅቶት ሳይሆን ጀዝቦ ከረሳው ብቻ ነው የማይኖረው ወይም ሲንዘላዘል። ሑሉም ሰው ከሕንፃው መውጣቱ ከተረጋገጥ ቡኃላ የእሳት አደጋ ሰራተኞች ወደ ሕንፃው ገቡ።ታዲያ በደውሉ ምክንያት ከየክፍሉ ተሯሩጠን ውጭ ስንሰበሰብ ሁሉንም ለመቃኘት ስሞክር አብዛኞቹ የውጭ አገር ዜጎች ነን።

በከተሞቻቸው የሚኖር ቀላል ቁጥር ያልሆነ የውጭ አገር ዜጋ እንዳለ ለማወቅ ዋና ከተማዋን ለአንድ ቀን መጎብኘት ብቻ ይበቃል። ከአዲስ አበባ አምጥቼህ መኃል ፒያሳቸው ውስጥ ብለቅህና ገምት ይህ አገር የማን ነው? ብዬ ብጠይቅህ የነጭ አገር አትጠራልኝም። ግምትህ ወይ ወደ አሜሪካ ወይ ወደ ደቡብ አፍሪካ ያዘግማል። እንዲያውም ትንሽ ቁጭ ካልክ አገርህ የምታውቀውን አንድ ከርታታ ስደተኛ ልታይ ትችላለህ። አላየኝም ብለህ ስሙን ብትጣራ ላይሰማህ ይችላል ወይም እንዳልሰማ ሊያልፍሕ ይችላል። ነገር አልገባ ብሎህ ሮጠህ  አቅፈህ መሳም ካማረህ ነገር ልታበላሽ ስለምትችል አርፈህ ብትቀመጥ ይሻልሃል።

እሳት የለም ተብለን ወይ በሲጋራ ወይ በሻማ ጭስ የተነሳው ደውል ከጠፋልን ቡኃላ ወደ ክፍላችን ገብተን ትምህርታችንን መኮምኮም ጀመርን። አስተማሪ በየሳምንቱ ይቀያየራል። በየትምህርቱ ርዕስ አዲስ አስተማሪ ይመጣል። ታዲያ በዛን ቀን የነበረው አስተማሪ ግምቴን ወደ ሕንድ ወሰደው። 15 ደቂቃ የተሰጠንን እረፍት በወንበሬ ላይ ተጎልቼ ወደአገርህ በሃሳብ ነጉጄ ሳለ አስተማሪዬ እፊቴ ተገትሮ ያልሰማሁትን ጥያቄውን ጠይቆኝ ኖሮ እንድመልስለት ይጠብቃል። ሲሪላንካዊ እንደሆነና መቀሌ ዩኒቨርሲቲ

ማስተማሩን ነግሮኝ ደስ የሚል አገር እንዳልኝ አስታውቆኝ ወደ መድረኩ ተመለሰ። እርሻና ኢንቫይሮመንት የሚሰጥበት ዩኒቨርሲቲ ስለሆን አገርህ ኢትዮጵያ በየምሳሌው አለች። በርኃብ፣ ለም መሬቷ፣ ቡናዋ፣ አለማያ ዩኒቨርሲቲ በቃ ትምህርቱ ወደ ግብርናና ኢንቫይሮመንት ካጋደለ ምሳሌዋ ማጣቀሻዋ አገርህ ነች። ታዲያ እንዳትታበይ አብዛኞቹ የሚያነሷት በክፉ ነው፣ የ77ቱን ድርቅ ፎቶ አምስት በዘጠኝ በሆነ ስክሪን ላይ ሲደቀንልህ ትምሕርትህን ትተህ በኃፍረት ጥፍርህ ውስጥ ትገባለህ።

በትምህርትቤታቸው ውስጥ የሚማረው አብዛኛው የውጭው ሰው ነው። እዚህ ትምህርት ሸጋ ነው። ሁሉም ሙሉ ነው። ለማንበብ መጽሃፍ ፈልገህ ካጣህ ይገርማል። 17 ዩኒቨርሲቲዎች 24 ዩኒቨርሲቲ ኮሌጆች አሉ የግል ዩኒቨርሲቲ ኮሌጆች ሳይቆጠሩ ይህ ሁሉ ለ5 ሚሊዮን ሕዝብ ነው። የፈለከውን መፅሃፍ አንላይን ሆነህ ማዘዝ ብቻ ነው። አገርውስጥ ስለሚኖር ያለህበት ድረስ ያመጡልሃል። አንተ ማንበብ ፈልግ እንጂ።

በትምህርት ጥራት ባይታሙም እኔ ግን በፈተናቸው ቅለት አማቸዋልሁ። አንድ ነገር አዙሮ ማሰብ ክልክል ነው። አንዳንዴ 10 የፈተና ጥያቄዎች በክላስ ፍሮንቴር ላይ ይለጥፋልሃል ክፍል ገና እንደተጀመረ። ከፈለግህ ጥያቄዎቹን መስራትና ለፈተና መቀመጥ ወይም የሚሰጡህን የትየለሌ የማጣቀሻ መፅሃፍትና ሌክቸር ኖት ማንብ፤ መምረጥ ያንተ ፋንታ ነው። ሴሚስተሩ ሲጀመር ከተሰጡት 10 ጥያቄዎች ውስጥ አስተማሪው 6ቱን መርጦ ለፈተና ያቀርባቸዋል። ከቀረቡት 6 ጥያቄዎች ውስት 4ቱን መርጠህ እንድትሰራ ያዝሃል። ያን ጊዜ ያሳለፍካቸውን ጥንብ ጥንብ ፈተናዎችና አንተም አስተምሪ ከነበርክ ያወጣኃቸውን ጥያቄዎች እያሰብክ 3 ሰዓት የተመደበለትን ፈተና በ45 ደቂቃ አጠናቀህ ወደቤትህ። ያውም 6ቱንም ጨርሰህ። በሶስት ኮፒ የሰራኃውን መልስ አንዱን ኮፒ ለግልህ አስቀርተህ ሁለቱን አስረክበህ ውልቅ ማለት ነው። ተርም ፔፐር ወይም አሳይመንት በትክክል ካስረከብክ (እዚህ ላይ ዘዴኞች ናቸው፣ ማወቅ ያለብህን ሳታውቅ አታልፋትም ሳትጨናነቅ ያሳውቁሃል)ፈተናውን በወሰድክ በሶስተኛው ቀን ስቱደንት ዊብህን ከፍተህ ውጤትህን ማየት ትችላለህ። በውጤትህ አታፍርም በጣም ስራ የሚበዛብህ አይነት ሰው ብትሆንም።

በአመለካከትና በአመጣጥ ትውልድ በተከፋፈለው የዚህ አገር የስደት ሂደት ውስጥ ተስፋ የሚሰጥ ነገር ባይኖርም ጥቂት ያልባከኑ ተስፋዎችን ከበርካታ ብኩኖች መሃል ልታይ ትችላለህ። እንደእድል ከነዚህ ተስፋዎች መሃል የሚጥልህ ካገኘህ በጥቂቱም ቢሆን የተሻለ የስደት ሕይወት ትፅፋለህ። ልምዳቸውን ያሳዩሃል፣ የሚፅፉትን የማንበብ እድል ይኖርሃል፣ በሰጣ ገባቸው ትማራለህ። ከኑሮ ውጣ ውረድና ከቤተሰብ ያልተረፈ ጊዜያቸውን ላገር ለወገን ሲያተርፉ ስትመለከት የሙሉ ጊዜ ቦዘኔ ሆነው የሰው ምስል ሲያተራምሱ ለሚውሉት የአገርህ ብኩን አዋልዶች ታዝናለህ።

ተስፋዎቹ ያገር የወገን መከራ እያንገበገባቸው ካቅማቸው በላይ ያለሙያቸው ላገር ለውጥ ሲጥሩ 24×7 ጊዜያቸውን በፌስቡክና በቻት ሱሰኞች ሆነው በጣታቸው ላይ የፌደላቱ ቀለም ታትሞ እስኪቀር ኪቦርድ ሲደበድቡ የሚውሉትን ስትመለከት ምን እንደሚሰማህ፣ በልማታዊ ድራማ ተጠምደው ኢሳትን አለማወቃቸው ሳያሳፍራቸው ሲቀር ምን እምደምትል አስበው። እንዲህ ማሰብህ ግን አይቀርም፥ ድሮ ድሮ ኢትዮጵያዊ ክቡር፣ ቅዱስ፣ ንፁህ ነበር፤  ኢትዮጵያዊ ጠቢብ፣ ፈላስፋ፣ ጀግና ነበር። የአሁኑ ኢትዮጵያዊ ምን ነክቶታል? ስደተኛው ምን ሆኗል? ማለትህ አይቀርም። በራስህ ሣይሆን በቀደሙት አባቶችህ ምክንያት ከሌላው ስደተኛ መለየትህን ታስባለህ፣ የነሱን ደም ስለያዝኩ በአካል ብሰደድም ልቤ አልተሰደደም ትላለህ፣ ብቻዬን ሳይሆን ምግባቸውን ይዤ ተሰድጃለሁ ትላለህ። መጋደል ቢያቅትህም ተጋድሏቸውን ታስባለህ። አገሬ አገሬ ትላለህ፣ ቤተሰብህን፣ ጓደኞችህን፣ ክብርህን ትናፍቃለህ።
*ትዘፍናለህ*

*አገሬ ገባለሁ*
*ድሪቶ አወልቃለሁ-ባርኔጣ ጥላለሁ*
*እሳት አገሬ ላይ-ክብሬን እሞቃለሁ*
*የሜርኳትን ትዝብት-ቁጭ ብዬ አነባለሁ*
*እያልኩ ሳወራ-ወራቶች አለፉ*
*ለካስ የኔም ስደት-ወሬ ሆኗል ትርፉ*
*እላለሁ ትላለህ*

ሰሎሞን አ.
negasi08@gmail.com